ኢትዮጵያ
አጭር የጥናት መግለጫ 3

Young Lives unicef

# በኢትዮጵያ የለጋ ልጅነት ትምህርትን ማሳወቅ፤

## ከያንግ ላይቭስ የዜሮ ክፍል መርሃ ግብር ጥናት የተጠናቀሩ ጥልቅ ዕይታዎች

### አንኳር ግኝቶችና ነጥቦች

- በቅርቡ የታየው ፈጣን የዜሮ ክፍል መስፋፋት፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ሁሉንም በቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ህጻናትን መሸፈኑ፣ በገጠር አካባቢዎች፣ በድሃ ቤተሰቦችና በኢትዮጵያ አዳጊ ክልሎች ለሚገኙ ህጻናት፣ ጠቃሚ የእኩልነት ትርፎች ያሉት ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ሆኖም፣ ይህ ፈጣን ዕድገት ጉልህ ልዩነቶችን የሚሸፍን ሲሆን በሚሰጠው ትምህርት ጥራት ዙሪያ ጥያቄ ያስነሳል።

- ከልጃገረዶች የበለጠ ወንዶች ዜሮ ክፍል እየገቡ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ረገድ የፆታ እኩልነትን ማሳካት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጀርባ ያለውን ምክንያትና የወላጆችን ዓላማ የበለጠ መረዳት ያስፈልጋል፤ ለልጃገረዶች ከፍተኛ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት አቅርቦት መስፋፋትም ይገባዋል።

- ዜሮ ክፍል፤ የ6 ዓመት ሕጻናት ለአንደኛ ክፍል ዝግጁ እንዲሆኑ እንደ ቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዓመት የታለመ መርሃ ግብር ነበር። ሆኖም ከትግራይ ክልል በቀር፣ የ4 እና 5 ዓመት ሕጻናትም የዜሮ ክፍል መርሃ ግብርን ሲከታተሉ ተስተውሏል፤ ብዙውን ጊዜ ደግሞ በአንድ ክፍል ውስጥ። ይህ ወላጆች የቅድመ መደበኛ ት/ቤት አገልግሎት እንደሚፈልጉ የሚያመላክት ማስረጃ ቢሆንም፣ ዕድሜን ያማከለ ትምህርትንና የመምህራንን በተለያዩ ዕድሜ ላይ ያሉ ሕጻናትን የማስተማር አቅምን በተመለከተ ስጋት ይፈጥራል።

- የዜሮ ክፍል ሥልጠና በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ከተመሰረተው የ3 ዓመት የመዋዕለ ሕጻናት ሥርዓተ ትምህርት ያነሰ ትኩረት ነው የተሰጠው። ለዜሮ ክፍል ሥርዓተ ትምህርትና ሥልጠና የተጠናከረ የቅድምያ ትኩረት መስጠት፣ ከመዋዕለ ሕጻናት ጋር ያለውን ልዩነት ለመድፈን ጠቃሚ ነው።

- የዜሮ ክፍል መምህራን እጥረት በአንድ ክፍል ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ህጻናት እንዲማሩ ያደረገ ሲሆን የአሳላጮች በዝቅተኛ ክፍያ በጊዜያዊነት መቀጠር፣ በቂ ካልሆነ ሥልጠና ጋር ተዳምሮ፣ ተነሳሽነትን አሳጥቷቸዋል። የመምህራንና አሳላጮች ሥልጠናን (የሥራ ላይ፣ የማሻሻያ፣ የክረምትና የርቀት ሥልጠና አማራጮች መስጠትን ጨምሮ) ማሻሻል የቅድምያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

- ዜሮ ክፍሎች ብዙ ጊዜ ጥራታቸውን ባልጠበቁ አካባቢዎች መገኘት ወይም ረዥም ጉዞን የሚጠይቁ መሆን የወላጆችና



ፎቶ ማስታወሻ፦ አንቶንዮ ፊዮረንቲ

ሕጻናትን ፍላጎት ያዳፍናል። መሰረተ ልማቶችን ለማሻሻል የበለጠ አትኩሮት መስጠት ያስፈልጋል፤ እነዚህም ከመጀመሪያ ደረጃ ክፍል አካባቢዎች የተለየ ተደራሽነት፣ ትክክለኛ መስኮቶችና የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ያላቸው ክፍሎች፣ ዕድሜን ያማከሉ ዴስኮችና ወንበሮች፣ ንፁህና አስተማማኝ የመፀዳጃ ክፍሎችና የውሃ አገልግሎት፣ የቤት ውስጥና የውጭ የመጫዎቻ ቦታዎችና ቁሳቁሶች፣ የማረፊያ ቦታዎችና ፍራሾች፣ ለአሳላጮች በቂ የሆኑ ተገቢ መጻሕፍትና መምሪያዎች እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕጻናት ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ይጨምራሉ።

- በተለይ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ሕጻናት ትምህርታቸውን ይከታተሉ ዘንድ ለማበረታታትና ቀኑን ሙሉ እንዲውሉ ለማድረግ የት/ቤት ምገባ አስፈላጊ ነው። የት/ቤት ምገባ አለመኖር፣ በዘላቂነት አለመቀጠል ወይም ዝቅተኛ ጥራት ያለው መሆን ለተማሪዎች ቁጥር ማሽቆልቆል ምክንያቶች ነበሩ። ለዜሮ ክፍል ትክክለኛ የት/ቤት ምገባ መስፋፋት ይገባዋል።

- በቅድመ መደበኛ - ት/ቤት አቅርቦት ረገድ፣ የአንድ ዓመቱ ዜሮ ክፍል፣ በከተማ አካባቢዎችና ከተደላደለ ቤተሰብ ለወጡ ህጻናት ከተዘጋጁት የ3 ዓመት መዋዕለ ህጻናት ይለያል። ዜሮ ክፍል፤ የት/ቤት ዝግጁነትንና እኩልነት ማስፈንን የማረጋገጥ አቅሙን እውን ያደርግ ዘንድ፣ ጥራትን ለማሻሻል ከሚወሰዱ እርምጃዎች በተጨማሪ፣ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት መርሃ ግብሮች የሚወስዱት ዓመታት ቁጥርን የመጨመር አማራጮችና የእነዚህ የባጀት አንደምታዎች በልዩ ትኩረት ሊጤኑ ይገባል።

## የለጋ ህጻንነት ዕድገት እንደ አለማቀፍ የቅድምያ ትኩረት


ለጋ የህጻንነት ዘመን፤ እንደ ወሳኝ የሕይወት ምዕራፍና ለፖሊሲ ቀረጻ፣ እንደ ቅድሚያ ትኩረት፣ ይበልጥ ዕውቅና እያገኘ መጥቷል። ቀደምት መርሃ ግብሮችን ተከትሎ፤ የለጋ ህጻንነት ዕድገት ፋይዳ፣ በዘላቂ ልማት ግብ ትኩረት 4.2 ላይ የተጠቆመ ሲሆን በ2030 አገራት ‹ወንዶችና ሴቶች ሕጻናት ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ ጥራት ያለው የለጋ ህጻንነት የዕድገት ክትትል እንዲሁም ክብካቤና የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ› እንዳለባቸው ይገልጻል። ጥራቱን የጠበቀ የለጋ ህጻንነት ትምህርት ማግኘት፣ የሕጻናትን የመደበኛ ትምህርት ዝግጅት ለማሻሻል ውጤታማ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ሲሆን፤ በለጋ ዕድሜ ትምህርት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት፣ በረዥም ጊዜ ውስጥ ለዳበረ ሰብአዊ ሀብት መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያበረክት ከፍተኛ ውጤትን እንደሚያስገኝ ተረጋግጧል። የያንግ ላይቭስ ጥናት በኢትዮጵያ፣ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት በጎ ውጤቶች፣ በዕውቀት አቀባበልና ት/ቤትን በማጠናቀቅ ሊረጋገጥ እንደሚችል ይጠቁማል[1]።

## በኢትዮጵያ በቅርቡ የታየው ፈጣን የቅድመ መደበኛ ት/ቤት የቅድምያ ትኩረት

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ተደራሽነት በእጅጉ ውስን ነበር፤ በገጠር አካባቢዎች ከሞላ ጎደል አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ በእርግጥ የቄስ ት/ቤቶች፣ ማንበብና መጻፍን በማስፋፋት ረገድ የተጫወቱት ሚና አሌ አይባልም። በከተማ አካባቢዎች፣ ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች፣ በአብዛኛው ሲተዳደሩ የነበሩት በግሉ ዘርፍ ሲሆን ከተደላደለ ቤተሰብ የወጡ ሕጻናትን ተጠቃሚ አድርገዋል፣ ምንም እንኳን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጫወቱት ሚና ቢኖርም። የያንግ ላይቭስ የ2006 የቤተሰብ ቅኝታዊ ጥናት መረጃ፣ ከ2ሺ በለጋ የዕድሜ ክልል ውስጥ ከነበሩ ሕጻናቶቻችን መካከል፣ አገልግሎቱን ያገኙ መኖራቸውን ፍንጭ ይሰጣል። በወቅቱ በከተማ አካባቢዎች የሚኖሩ 58 በመቶ ገደማ በለጋ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕጻናት፣ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት መርሃ ግብርን ተከታትለዋል፤ ነገር ግን በመንግሥት የሚተዳደር መርሃ ግብር ውስጥ የገቡት 5 በመቶ ያህሉ ብቻ ነበሩ። በአንጻሩ፣ ማናቸውንም ዓይነት የቅድመ መደበኛ ት/ቤት መርሃ ግብር የተከታተሉ የገጠር ሕጻናት ከ4 በመቶ የሚያንሱ ናቸው (Woodhead et al. 2009)። የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት፣ በ2010 ከነበረው 5 በመቶ ገደማ፣ በ2016 ወደ 46 በመቶ ያደገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ዜሮ ክፍል፣ 33 በመቶ አስተዋጽኦ አድርጓል (MOE 2018)።

ስትራቴጂካዊ የአሰራር ዕቅድና መመሪያዎች የተከተለው፣ የለጋ ልጅነት ክብካቤና ትምህርት - Early Childhood Care and Education (ECCE) የበይነ ሚኒስትሮች ብሔራዊ ፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ጉልህ ለውጥን የሚወክል ሲሆን መንግስት ለECCE አቅርቦት ፈጣን ዕድገት ማቀጣጠያ አቅርቧል፡፡ በሁሉም የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ዓይነቶች፣ የተመዘጋቢ መጠን፣ በአምስት ዓመት ውስጥ በዘጠኝ እጥፍ አድጓል[2]። እነዚህም የሕጻን - ለሕጻን መርሃ ግብሮች[3]፣ ከሁለት ዓመት በላይ የመዋዕለ ሕጻናት ፕሮግራሞች እንዲሁም የተፋጠነ የት/ቤት ዝግጁነት መርሃ ግብሮችን[4]

ምስል 1፡- የመዋዕለ ሕጻናት፣ የዜሮ ክፍል እና የሕጻናት ለሕጻናት ምዝገባ፣ ከ1999/00 እስከ 2014/15




ምንጭ፡- Woodhead et al. (2017).

1 ቅድመ መደበኛ ትምህርት መከታተል በቃላትና በሂሳብ ለሚለካ የዕውቀት መዳበር አስተዋጽኦ እንዳለው የታየ ሲሆን፤ በ5 አመት ላይ የታዩ ልዩነቶች በ8 አመት ላይ ጉልህ መሆናቸው ቀጥሏል (Woldehanna 2016))። በተጨማሪም በከተማ የሚገኙ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተከታተሉ ልጆች ሁለተኛ ደረጃን ለማጠናቀቅ 25 በመቶ የበለጠ እድል አላቸው። ይህም ልዩነት የሁለት አመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለተከታተሉ፣ በተለይም የሦስት አመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለተከታተሉ ከፍተኛ ነበር (Woldehanna and Araya 2017)።

2 በ2009/10 የትምህርት ዘመን ከነበረው 340,000፣ በ2014/15 ከ3 ሚሊዮን በላይ (Rossiter 2016)።

3 በዩኒሴፍ የሚደገፈው ይሄ የመንግስት መርሃ ግብር በክፍል ደረጃቸው ከፍ ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ታናናሾቻቸውን የሚያስተምሩበት ነው።

4 ይሄ መርሃ ግብር መምህራን በቅድመ መደበኛ ዕድሜ የሚገኙ ሕጻናትን አንደኛ ክፍል ከመጀመራቸው በፊት ባለው የክረምት የዕረፍት ጊዜ የሚያዘጋጁበት፤ ወይም የትምህርት አመቱ እንደተጀመረ መምህራን ጥልቀት ያለው ትምህርት የሚሰጡበት ነው።

ያካትታሉ። ሆኖም ትልቁ ዕድገት የተገኘው በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከተቋቋመው የመንግሥት የት/ቤት፣ የዜሮ ክፍል፣ የዝግጁነት ዓመት ነው (ምስል 1)።

ቅድመ መደበኛ ት/ቤትን የማስፋፋት አስፈላጊነት በ2015 በወጣው 5ኛው የትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራም (ESDP V) ውስጥ የተጠቀመ ሲሆን መንግሥት የግል ዘርፍ አገልግሎት ሰጪዎችን ከማቀናጀት ሚናው በተጨማሪ "በቅድመ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት፣ ከመምህራን እስከ መማሪያ ክፍሎች እንዲሁም የመማሪያ ቁሳቁሶች ድረስ ሙሉ በሙሉ ይሳተፋል" ሲል በአጽንኦት ይገልጻል፤ ከ4-6 ዓመት ዕድሜ ያሉ ሕጻናት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ምዝገባ ግብን ወደ 80 በመቶ ለማድረስ። 5ኛው ትምህርት ሴክተር ልማት ፕሮግራም ፣ በተጨማሪም፣ የመንግሥት የቅድመ መደበኛ ት/ቤት አቅርቦት፣ የት/ቤት ዝግጁነት መሰረታዊ ክህሎቶችን በማዳበርም ሆነ እኩልነትን በማስፈን ረገድ ወጪ ቆጣቢ እንደሆነ ያምናል።

## የያንግ ላይቭስ ጥናትና ከት/ሚኒስቴር ጋር ያደረገው ተሳትፎ

ያንግ ላይቭስ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የ3ሺ ሕጻናትን ሕይወት በጥልቅ ተከታትሏል፤ በአምስት ክልሎች በ20 አካባቢዎች የሚኖሩ በሚሊኒየሙ መባቻ ላይ የተወለዱ በለጋ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ 2 ሺ ሕጻናትና ሰባት ዓመት ቀደም ብለው የተወለዱ ከፍ ባለ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ 1ሺ ሕጻናትን። ጥናቱ፤ ድህነት፣ የኑሮ ልዩነቶች፣ ምግብና ጤና፣ ትምህርት፣ የሕጻናት ከለላ፣ ወጣትነትና ጾታን ጨምሮ መጠነ ሰፊ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችና የዕድሜ ክልሎች ላይ ጠንካራ የፖሊሲ ቁርጠኝነት የያዙ የአገር ውስጥ የጥናት አጋሮችን ያሳተፈ ነበር። ያንግ ላይቭስ፣ በሕጻናት ጥናትና ትግበራ ፎረም አማካኝነት፣ ከሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ጋር ሰርቷል።

በያንግ ላይቭስ ጥናት ውስጥ ያሉ ሕጻናት ሲያድጉ፣ ያንግ ላይቭስ በትምህርት ላይ የሚያደርገው ጥናት አስፈላጊነቱ ይበልጥ እየጨመረ መጥቷል። ያንግ ላይቭስ ቀደም ሲል የቅድመ መደበኛ ት/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መስፋፋት ከ2006 - 2010 ምን እንደሚመስል አጥንቷል። (Orkin, Yadete and Woodhead 2012) ያንግ ላይቭስ፣ በ2015 ከቻይልድ ኢንቨስትመንት ፋውንዴሽን ፈንድ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ፣ የECCE ጥናትን ጀምሯል። ይህ ከትምህርት ሚኒስቴር ESDP V ማርቀቅ ጋር የተገጣጠመ ሲሆን ያንግ ላይቭስ የECCEን ESDP V ዕቅድ ዝርዝሮች ለማሳወቅ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ ግብአት መስጠት ችሏል። ከESDP V አርቃቂ ቡድንና ከሌሎች የትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣናት እንዲሁም ከትላልቅ ECD/ECCE ተኮር ለጋሾችና መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ካደረጉ (በተለይም ዩኒሴፍ፣ ዓለም ባንክና ሴቭ ዘ ችልድረን) መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ትስስሮች ተፈጥረዋል። ለዎርክሾፕ የቀረበ ጥናት በኋላ ላይ ወደ ፖሊሲ ወረቀት ያደገ ሲሆን ስድስት ውጤታማ የECCE አሰራሮች ገጽታዎችን ለይቶ አስቀምጧል፦

(i) ፍትሃዊና አካታች ተደራሽነት፣ (ii) ሥርዓተ ትምህርት፣ የማስተማርያና መማርያ ቁሳቁሶች፣ (iii) መምህራንና የት/ቤት መሪዎች፣ (iv) የወላጅና ማህበረሰብ ድጋፍና ተሳትፎ፣ (v) መመዘኛዎች፣ ክትትልና ትምህርት፣ እንዲሁም (vi) አሰራሮች፣ ፋይናንሲንግ፣ አስተዳደርና አመራር (Rossiter 2016)።

የትምህርት ሚኒስቴር የዜሮ ክፍል አገልግሎትን ለማስፋፋት በሚያደርገው ጥረት ለመደገፍ፤ ያንግ ላይቭስ የሚከተሉትን ነጥቦች የተሻለ ለመረዳት፣ ከትምህርት ቤት ማሻሻል ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች ጋር በሦስት ምዕራፎች ሰርቷል፦ (1) የዜሮ ክፍል ጅማሮ፣ የተገኙ መረጃዎችን በመተንተንና በ7 ክልሎች በሚገኙ ክልላዊ የትምህርት ቢሮዎች የምክክር ጉብኝት በማድረግ፤ (2) የመምህራን ሥልጠና አቅርቦት፣ በአንድ ክልል የሚገኙ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችን በመጎብኘት፣ እንዲሁም (3) የለጋ ዕድሜ ትምህርት ፍላጎት፣ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ የያንግ ላይቭስ አካባቢዎች፣ ይዘት- ተኮር ዓይነተኛ ጥናት በማካሄድ።

## የለጋ ዕድሜ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ የተስተዋሉ ክልላዊ ልዩነቶች


በዜሮ ክፍል አቅርቦት ተደራሽነት፣ በዜሮ ክፍል ምዝገባ የለውጥ መጠን፣ የምዝገባ ሁኔታ በፆታ፣ በአካባቢና በዕድሜ ረገድ ያለውን ክልላዊ ልዩነት ለማየት፣ የብሔራዊ ትምህርት ኢንፎርሜሽን ሲስተም መረጃ ትንተና ከSIP ECD ባለሙያዎች ጋር ተከናውኗል። ታዳጊ ክልሎች፣ ከዝቅተኛ መነሻ፣ ቀላል የማይባል የምዝገባ መሻሻል ማምጣታቸውን ትንተናው አመልክቷል። በእጅጉ የተጠናከሩ ክልሎች፤ በጠንካራ የማህበረሰብ ተሳትፎ ስኬታቸውን አጠናክረዋል፤ ከተወሰኑ ክልላዊ ልዩነቶች ጋር፡፡ ትግራይ ከፍተኛ ምዝገባ የተስተዋለበት ሲሆን፣ በአንፃሩ አዲስ አበባ ከመዋዕለ-ህፃናት መለመድ አንፃር፣ የዜሮ ክፍል ማስፋፋት አላስፈለገውም። የመምህራን ሥልጠና ዕቅዶች በኦሮምያና አማራ ክልሎች የቅድምያ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። አማራ ክልል በምግብ አቅርቦት፣ በውሃና የንፅህና መሰረተ ልማት ግንባታም ላይ አተኩሯል - ከማህበረሰብ በተደረገ የቁሳቁስና የጉልበት አስተዋጽኦ። ክልሉ፣ ራቅ ባሉ አካባቢዎች የጉዞ ርቀትን ለመቀነስ፣ የዜሮ ክፍል መማሪያዎችን ለብቻቸው የመክፈት አዲስ አሰራርም ላይ ትኩረቱን አድርጓል።

ዜሮ ክፍል ያላቸው ት/ቤቶች መጠን፣ በአራት ዓመት ውስጥ፣ በ75 በመቶ ገደማ አድጓል (ምስል 2)[5]። ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፈጣን ዕድገት አስመዝግቧል፤ አምስት ክልሎች ግን 50 በመቶ ብቻ ዕድገት ወይም ጥቂት የዜሮ ክፍል ትምህርት የሚሰጡ ት/ቤቶች ነበራቸው።

በዜሮ ክፍል ምዝገባ የተስተዋለው አስደናቂ ዕድገት፣ ከፆታና ዕድሜ ጋር የተያያዙ ሁለት ወሳኝ አዝማሚያዎችን ጋርዷል። አንደኛ፤ በ2015 ዓ.ም. ከሴቶች በእጅጉ የሚልቁ ወንድ ህጻናት ነበሩ ዜሮ ክፍልን የተከታተሉት። በመላው የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፣ የ0.95 የፆታ ፍትሃዊነት ልዩነት ከመስተዋሉ አንጻር፣ በዘርፉ የፆታ እኩልነት ማሻሻልን ይፈልጋል።

5 በ2011/12 ከነበረው 60 በመቶ፣ በ2014/15 ወደ 70 በመቶ አድጓል።

**ምስል 2፦ ዜሮ ክፍል ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በመቶኛ (%)፣ በክልል ደረጃ፣ በአራት ዓመት ውስጥ - ከ2011/12-2014/15**





ምንጭ፦ Woodhead et al. (2017).

ሁለተኛ፣ የዜሮ ክፍል የመጀመሪያው ፖሊሲ ርዕይ፣ ለ6 ዓመት ዕድሜ ህፃናት፣ በ7 ዓመታቸው፣ 1ኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት፣ እንደ አንድ ዓመት መርሃ-ግብር የተቀረፀ ነበር። ሆኖም ዜሮ ክፍል የ3 ዓመት ህፃናት ተማሪዎችን ሳይቀር ሲያስተናግድ የቆየ ሲሆን ዜሮ ክፍል ከተመዘገቡት ተማሪዎች ውስጥ 42 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው በ6 ዓመት ዕድሜ ላይ የነበሩት። ሁኔታው ከክልል ክልል ይለያያል (ምስል 3)። በትግራይ ከዜሮ ክፍል ተመዝጋቢዎች ውስጥ 91 በመቶ ያህሉ በ6 ዓመት ዕድሜያቸው ላይ የነበሩ ሲሆን፣ በሌላ በኩል በሶማሊያና አዲስ አበባ ለምሳሌ፡- ከ25 በመቶ ያነሱ ተመዝጋቢዎች ናቸው በ6 ዓመት ዕድሜ ላይ የነበሩት። ይህ የዜሮ ክፍል በጣም ለጋ ህፃናትን የመሳብ አዝማሚያ (ሁኔታ)፣ ቤተሰቦች ለለጋ ዕድሜ የትምህርት ዕድሎች ያላቸው ፍላጐት አዎንታዊ ነፀብራቅ ተብሎ ሊተረጐም የሚችል ሲሆን ይህም በቅድመ ትምህርት ፍላጐት በኩል ተጨማሪ ጥናትን አነሳስቷል (ከታች ይመልከቱ)። ነገር ግን በአንድ ክፍል ውስጥ በተራራቀ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህፃናት መገኘት፣ ለህፃናት የእድገት ደረጃ የታለመውን የማስተማርና መማር ሂደት ለመበየንና ለመተግበር ፈታኝ ያደርገዋል።

## ያንግ ላይቭስ ከክልል የትምህርት ቢሮዎች ጋር ያደረጋቸው ምክክሮች

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓት፣ የመንግስት ፖሊሲዎች አፈፃፀምን ለየክልሎቹ ያከፋፍላል። በእያንዳንዱ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የክልል ት/ቢሮዎች፣ የፖሊሲ ግቦችን የማስፈጸም ቀዳሚ ኃላፊነት አለባቸው። የዜሮ ክፍል ጅማሮ የአፈፃፀም ልዩነትንና

**ምስል 3፦ የዜሮ ክፍል ምዝገባ ድርሻ፣ በክልልና በዕድሜ፣ 2014/15**




ምንጭ፦ Woodhead et al. (2017).

በዲሴምበር 2015 ለECCE ግብረ-ሃይል የቀረቡ የጥናት ግኝቶችን የበለጠ ለመረዳት፤ በሰባት ክልሎች ከSIP ECCE ባለሙያዎች ጋር የምክክር ጉብኝቶች ተደርገዋል[6]። ምክክሮቹ፤ የECCE አስተዳደሮች ስፔሻሊስት እጥረት በሚኖር ጊዜና በECCE ማስፋፋት ላይ ብሔራዊ ዕቅዶችን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ወይም ሥልጠና ሳይሰጥ ሲቀር፣ የተለጠጡ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን ለማስፈፀም ያሉትን ተግዳሮቶች ጠቁመዋል። ሆኖም፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ የምዝገባ ግቦችን ያስቀመጡ ሲሆን የአገልግሎት ፍላጐትን ለመገመትም የሥነ ህዝብ መረጃን ተጠቅመዋል። አንዳንድ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ለአርብቶ አደር ማህበረሰቦች፣ ለልጃገረዶችና አነስተኛ ተናጋሪ ባላቸው ቋንቋዎች የዜሮ ክፍል መርሃ ግብር ለመጀመር ግብ አስቀምጠዋል። ሁሉም የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ፍላጐትን ለማነሳሳት ተመሳሳይ አቅጣጫዎችን ተጠቅመዋል፤ በመንደር ደረጃ የሚደረጉ የንቅናቄ መርሃ ግብሮች።

የክልል ትምህርት ቢሮዎች ተመሳሳይ የማስፈፀም እንቅፋቶችም ገጥሟቸዋል። ለECCE አገልግሎቶች በጀት የተመደበለት አንድም ክልል አልነበረም። ይህም ንኡስ ዘርፉ እንዴት ሊስፋፋ ይችላል የሚለውን በተመለከተ ትልቅ ጥያቄዎች ያስነሳል። ሁሉም የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ብቃት ያለው ሰራተኛ እጥረት እንዳለባቸው እንዲሁም የECCE የአፈፃፀም ደረጃዎችን፣ የክትትልና ቁጥጥር ዘዴዎችን በተመለከተ በቂ መመሪያ እንዳላገኙ ገልጸዋል። የሰው አቅም እጥረት ወደ መማሪያ ክፍሎችም የደረሰ ሲሆን በተለይ የዜሮ ክፍል መምህራን፣ ብዙውን ጊዜ ያልሰለጠኑና ከየአካባቢው የተቀጠሩ ወይም ከዝቅተኛ የመጀመሪያ ደረጃ ክፍሎች የተመደቡ ይሆናሉ።

ከክልል የትምህርት ቢሮዎች ጋር የተካሄዱ ውይይቶችና የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተም መረጃ ትንተና፤ ዕቅዶችንና የምዝገባ ሁኔታዎችን አስመልክቶ በርካታ ነጥቦችን ጠቁሟል፤ እነዚያንም ያንግ ላይቭስ ለት/ሚኒስቴር ኃላፊዎች፣ ለSIP እና ለECCE ግብረ ሃይል መልሶ ሪፖርት አድርጓል። ለምሳሌ፡-

- የሚጋሯቸው የጋራ ጉዳዮች ባላቸው ክልሎችም ሳይቀር ክልላዊ ልዩነቶች ለመፈጠሩ ምክንያቱ ምንድን ነው? ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ራቅ ባሉ አካባቢዎች፣ ዜሮ ክፍልን በከፍተኛ ቁጥር ተደራሽ ማድረግ ችሏል። ሌሎች ታዳጊ ክልሎች በESDP V ግቦች ረገድ ግስጋሴ ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ የአሰራር እቅዶች መማር ይችሉ ይሆን?
- በትግራይ የ6 ዓመት ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ከመቀላቀላቸው በፊት ለዜሮ ክፍል በመመዝገብ ረገድ የታየው ጉልህ የአፈጻጸም ስኬት፣ ዕድሜን ያማከለ፣ የECCE ክልላዊ ስትራቴጂ አካል ነውን? መሰል ስትራቴጂ በሌላም አካባቢ ይሰራ ይሆን?
- የዜሮ ክፍል መርሃ ግብር የተቀረጸው ለማነው? የ6 ዓመት ህፃናት መርሃ ግብር ሆኖ የሚቀጥል ከሆነ፤ ተደራሽነቱን ለዚህ ቡድን ብቻ ለመገደብ እንዲሁም ለ4 እና 5 ዓመት ህፃናት ተጨማሪ፣ ዕድሜን ያማከለ የለጋ ዕድሜ የትምህርት ዕድሎችን ማቅረብን ለማጤን የበለጠ መሰራት ይኖርበታል።
- በአሁኑ ወቅት ሴት ህፃናት በዜሮ ክፍል ውስጥ በቅጡ ካለመወከላቸው አንፃር፣ እንዴት ነው የፆታ እኩልነትን ማጠናከር የሚቻለው?

ብዙ ጥያቄዎች ሳይመለሱ ቀርተዋል፡፡ የጥናት፣ ክትትል፣ ግምገማና የቁጥጥር አሰራሮች፣ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ገና በእንጭጭ ደረጃ ላይ ናቸው፤ ስለዚህም ለመሰረታዊ መረጃ አንገብጋቢ ፍላጐት አለ፤ በተለይም በዜሮ ክፍሎች ውስጥ ስለሚሰሩ መምህራን አቅምና ክህሎት፣ በተጨባጭ ምን ሥርዓተ ትምህርትና ሥልጠና እየተገበሩ እንዳሉ፣ በመማርያ ክፍል ውስጥ ምን ግብአቶች እንደሚገኙ እንዲሁም ስለ ህፃናት ትምህርትና ለመደበኛ ትምህርት ስላለው ዝግጁነት።

## ያንግ ላይቭስ በዜሮ ክፍል መምህራን አቅርቦት ላይ ያደረገው ጥናት

ከክልል ትምህርት ቢሮ ምክክሮች የተጠናቀሩ ግኝቶች በቀረቡበት ወቅት፣ የሰው ሃይል አቅም ጉዳይ ወሳኝነቱ አሌ የማይባል ሆኗል፡- ፈጣን ዕድገት እያሳየ ያለውን የዜሮ ክፍል ምዝገባ፣ ክልሎች እንዴት ነው በሰለጠኑ መምህራን የሚሞሉት ? እና የተገመተውን የ100 ሺ ተጨማሪ መምህራን ፍላጎት ለማሳካት ምን ዕቅዶች ናቸው የሚያስፈልጉት?

በ2016 መጀመሪያ ላይ ያንግ ላይቭስ፣ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ ጥናት፣ በአማራ ክልል፣ ከSIP ባለሙያዎች[7] ጋር አካሂዶ ነበር። አማራ ክልል በቅርብ ዓመታት፣ ትልቁን የዜሮ ክፍል ምዝገባ ዕድገትና ከፍተኛ ቁጥር ያለው የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች አስመዝግቧል፤ ከአገሪቱ 36 ኮሌጆች ውስጥ አሥሩ፤ ምንም እንኳን ከእነዚህ ውስጥ የECCE ሥልጠና የሚሰጡት 17ቱ ብቻ ቢሆኑም። አማራ ክልል፤ በESDP V ወቅት፣ 100 ፐርሰንት የሰለጠኑ የECCE ሰራተኞችን ለማፍራት ማለሙን አስታውቋል። ሦስት ዋነኛ ጉዳዮች በእንቅፋትነት ተለይተዋል፡-

### ከላይ ወደ ታች ዕቅድ እና ደካማ ተግባቦት

በአምስት ዓመት ውስጥ 20 ሺ ገደማ የECCE መምህራንን ለማሰልጠንና ለመመደብ ከተያዘው ክልላዊ ዕቅድ ጋር፣ ለECCE የአማራ መምህራን ሥልጠና አሰራርን ለማሳደግ ዕውቅና እና ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ ነበር። ሆኖም ይሄ ግብ፣ አሁን ባሉት መርሃ ግብሮች፣ ዕቅዶችና ግብአቶች እውን እንደማይሆን የምልከታ ሥራ ጠቁሟል።

6 ቃለ መጠይቅ ለክልል ትምህርት ቢሮ አስተዳዳሪዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ቀርቦ ነበር፦ (i)ለECCE ያላቸው ዝግጁነት (በክህሎት፣ በስልጠና እንዲሁም ከላይ በሚደረገው ድጋፍና ባለው አመለካከት፤ (ii)ያለፉት፣ ያሁኖቹ እና የወደፊቱ የECCE እቅዶቻቸው፤ (iii) ለECCE መምህራን የሚደረግ ስልጠና፣ ምደባ፣ ክፍያ እና የክትትል ሂደቶች፤ እና (iv) የECCE ክፍሎች ሊያሟሏቸው ስለሚገባቸው ደረጃዎች እና በአሁኑ ጊዜ ስላሏቸው ግብዓቶች።

7 በስድስት የወረዳ የትምህርት ጽ/ቤቶች እንዲሁም በክልሉ ከሚገኙ ከአስር የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መካከል በአራቱ ውስጥ ቃለ መጠይቆች ተደርገው ነበር። ቃለ መጠይቆቹ እንደ ECCE የሰልጣኞች መርሃ ግብሮች ሃላፊዎች፣ በከፍተኛ ደረጃ ከሚገኙ አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የECCE ስልጠና እየወሰዱ ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር እንዴት መምህራን እየተዘጋጁ እና እየተመደቡ እንደሆነ እንዲሁም ስለእውቀታቸው በተለይም ለዜሮ ክፍል ያላቸው አመለካከት ላይ ያተኮሩ ነበሩ።

የECCE ሥልጠና መርሃ ግብሮች የተዘጋጁት በአጠቃላይ በዲፕሎማ አሊያም በሰርተፊኬት ደረጃ ነበር። ግን በይዘት እንዲሁም በመግቢያና በመመረቂያ መስፈርቶች ረገድ ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል። አስተማሪዎችንም፣ ማንኛውም የተለየ አይነት የአገልግሎት አቅርቦት፣ የዕድሜ ክልል ወይም የኋላ ምደባ ላይ ሳያተኩሩ፣ ለ"ዩኒቨርሳል ECCE" ብቻ ነበር የሚያዘጋጁት። መምህራን፤ የፕሮግራም ሞጁልስ ከECCE ሥልጠና ጋር አግባብነት እንዳላቸው ጠቁመዋል፤ ነገር ግን ይዘቱ ንድፈ ሐሳብ የበዛው መሆኑና ከመጀመሪያ ደረጃ የስልጠና መርሃ ግብሮች ጋር በእጅጉ መደራረቡ ጥያቄዎች አስነስቷል። መምህራኑ ለECCE ሥልጠና የስፔሻሊስት ሞጁልስ አስፈላጊነትንም ተገንዝበዋል።

መምህራንም ሆኑ የECCE ሥልጠና መርሃ ግብሮች የሚመለከታቸው የአስተዳደር ሰራተኞች፤ ከፌደራል ወይም ክልላዊ መንግሥት ምን እንደሚጠበቅባቸው፣ የትኞቹ የሥልጠና አቅጣጫዎች ተገቢ እንደሆኑ፣ የትኛው ሥርዓተ ትምህርት ለሰልጣኞች መዋል ወይም በዜሮ ክፍሎች ወይም መዋዕለ ሕጻናት ማዕከሎች መተግበር እንዳለበት፣ ሥልጠና ያገኙ የECCE መምህራን ካለው የደሞዝ ስኬል ወይም የሙያ ዕድገት ዕድሎች ጋር እንዴት ይጣጣማሉ የሚሉትን ጨምሮ ጥርት ያለ ግንዛቤያቸውን አልገለጹም። አንድ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ አስተማሪ እንደገለጸው፤ የECCE ማስፋፊያ የተጀመረው "ግብአቶችም መምህራንም ባልተዘጋጁበት ሁኔታ በዘመቻ መልክ ነው"። ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተግባቦት ጋር በተገናኘ የማይታበሉ ድክመቶች ተስተውለዋል፤ ዋና የፖሊሲ ሰነዶችን ብርቅዬ በማድረግ።

የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች አንጋፋ አመራሮች፤ ራሳቸውን የሚቆጥሩት፣ በክልል ትምህርት ቢሮ በተነገራቸው መሰረት መምህራንን እንደሚያሰለጥኑ፣ ትዕዛዝ ፈጻሚዎች አድርገው ነው።

## *የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ የዜሮ ክፍል መምህራን ሥልጠናን የመደገፍ አቅም*

እነዚህ እንቅፋቶች ቢኖሩም ቅሉ፤ መምህራን ውስን አቅምን በመጠቀም፣ የECCE አቅምን ለማጠናከር ተነሳሽነት አሳይተዋል፡፡ ሀሳቦቹ፤ በECCE ዙሪያ መረጃ ለማጋራት ጊዜያዊ ኩነቶች ማዘጋጀት፣ በየወረዳው የሚገኙ የECCE መሰረተ ልማቶችን በመጎብኘት ልምድ መቅሰም፦ ‹‹ለምሳሌ እኔ በግሌ ከባቢውና የECCE አቅርቦት ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ የማህበረሰብ ት/ቤት ጎብኝቻለሁ፡፡ ይሄ በራሴ ተነሳሽነት ያደረግሁት ነው።" እንዲሁም ከሌሎች አገር አቀፍ የECCE አሰራሮች ለመማርና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ለማግኘት የኢንተርኔት ግብአቶችን መጠቀምን ያካትታሉ።

የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ከት/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በርካታ ጊዜያዊ ትስስሮችንና ግንኙነቶችን መስርተዋል። የመምህር ማሰልጠኛ ኮሌጆች ውስንነቶችንም ተገንዝበዋል፤ እናም የመርሃ ግብሩን ግቦችና በሁሉም ወገን ያሉ እንቅፋቶችን በተመለከተ ግንዛቤን ለማሻሻል ለሥልጠናና ግንዛቤ ዓላማዎች ከፌደራልና ክልል የECCE ዕቅድ አውጪዎች የቴክኒካል ትስስር ጠይቀዋል።

## *የቅድመ መደበኛ አገልግሎት ሥልጠናና የአገልግሎት ላይ ድጋፍ ሞዴሎች*

ምንም እንኳን የዕቅድና ቅንጅት አሰራሮች ሊሻሻሉ የሚችሉ ቢሆኑም፣ ብቃት ያላቸው መምህራንን ለማፍራት ያለውን ፍላጎት ለማሟላት፣ ልማዳዊና በአንጻራዊነት ውድ የቅድመ አገልግሎት ሥልጠና አቅጣጫዎች በቂ የመሆን ዕድላቸው አናሳ ነው። ሁለት ዋነኛ ተግዳሮቶች ሊቀረፉ ይገባል።

አንደኛ፤ ዜሮ ክፍል የሚታየው በኢትዮጵያ አብዛኞቹን ሕጻናት የመድረስ አቅም እንዳለው የECCE አቅጣጫ ተደርጎ ነው። ሆኖም ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መካከል፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የመማሪያ ክፍሎችን ለዜሮ ክፍል ማዋል ጊዜያዊ መፍትሄ ነው ከሚለው እምነት ጋር ተዳምሮ፣ ዜሮ ክፍልን የማስፋፋት ተፈጻሚነትን አስመልክቶ ጥርጣሬ ተንጸባርቋል። ይህን አመለካከት በሚደግፍ ሁኔታ፣ የማህበረሰብ ንቅናቄ ጥረቶች፣ ለዜሮ ክፍል፣ ፈጣን የመሰረተ ልማት መስፋፋትን አምጥተዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መማሪያ ክፍሎችን በመለወጥና አካባቢያዊ ግብአቶችን ተጠቅሞ ECCE-ተኮር መሰረተ ልማቶችን በመዘርጋትና በማቅረብ ፈጣን ስኬቶች ተገኝተዋል። ሙሉ አቅም ወዳለው የECCE ከባቢዎች መገስገስ ግን አዝጋሚ ይሆናል። በርካታ የመማርያ ክፍሎች ተበታትነው ወይም ለECCE በማያመች ሁኔታ ተለውጠው ቀርተዋል፤ በቂ የንጽህናና የውሃ አገልግሎት በአቅራቢያ ሳይኖራቸው እንዲሁም ብዙውን ጊዜ በቂ የተለየ የውጭ ቦታና የመጫወቻ ግብአቶች የሌላቸው ሆነው።

ሁለተኛ፤ የECCE መምህርነት ደረጃን ለመቀዳጀት የሰርተፊኬት ሥልጠና መርሃ ግብሮች፣ እንደ አንድ ዓመት (‹ፈጣን ጉዞ›) አቅጣጫ  መቀጠላቸውን አስመልክቶ ከፌደራልና ክልላዊ መንግሥታት ግልጽነት ያስፈልጋል። የሰርተፊኬት ሥልጠና በአጠቃላይ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ ለሦስት ዓመት ከሚሰጠው የዲፕሎማ ኮርስ ያነሰ ተደርጎ ነው የሚታመነው። ነገር ግን የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ መምህራን እጥረትን በሚፈለገው መጠን ለማሟላት እንዲሁም በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ በሺዎች የሚሰሉ ጊዜያዊና ብዙ ጊዜም ከየአካባቢው የሚቀጠሩ ግለሰቦች የአቅም ግንባታ ፍላጎቶችን ለመመለስ ይህን የረዥም ጊዜ ኮርስ የመተግበር ተጨባጭነት በጥያቄዎች የተከበበ ነው። ለመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የአጭር ጊዜ ሥልጠና አማራጮች - እንቅስቃሴዎች በሌሉባቸው ጊዜያት የሚሰጡ የክረምት ኮርሶችን የመሳሰሉት፣ ለተለጠጡ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት የሚሞክረውን አሰራር አቅም በፍጥነት ለማሳደግ ሊያግዝ ይችላል። ለእነዚህ ግለሰቦች የሙያ ማጎልበቻ ኮርስ ለመቅረጽ ሥራ የተጀመረ ሲሆን ይህም በሬዲዮ ወይም መሰረታዊ የክህሎት ሥልጠናን የያዘ "የመምህራን ጥቅል አገልግሎቶች"ን እንዲሁም ይበልጥ ተደራሽነት ያላቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚሰጥ ተደጋጋፊ አቅጣጫዎችን ሊያካትት ይችላል።

ያንግ ላይቭስ፣ በዜሮ ክፍል መምህራን አቅርቦት ላይ ባደረገው ጥናት ላይ ተመስርቶ፣ የECCE አፈጻጸምን ለማሻሻል፣ ስድስት ዋነኛ ተግዳሮቶችን የሚዘረዝር  ጽሑፍ አዘጋጅቷል። እነዚህም፦ ማስፋፋት፣ እኩልነት፣ ዕድሜን ማማከል፣ የተለያዩ ሴክተሮች ቅንጅት እንዲሁም ጥናትና መረጃዎች ናቸው (Woodhead et al. 2017)።

## በዜሮ ክፍል አገልግሎት አሰጣጥ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ዕይታዎች

የለጋ ዕድሜ ትምህርት ፍላጎትን በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ያንግ ላይቭስ፣ በተለያዩ ክልሎች[8] በሚገኙ አራት አካባቢዎች ላይ ጥናት አካሂዷል፡፡ ወላጆች፤ ዜሮ ክፍል፣ ሕጻናት፣ በአካባቢያቸውና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያነቡና እንዲጽፉ፣ ራሳቸውን ከት/ቤት ከባቢ ጋር እንዲያላምዱ፣ ለመምህር ተማሪ ግንኙነት፣ ለት/ቤት ደንቦች፣ ለዲሲፕሊንና የግል ንጽሕና አጠባበቅ አዲስ እንዳይሆኑ፣ ከሌሎች ሕጻናት ጋር እንዲጫወቱና እንዲግባቡ እንዲሁም ጥያቄ የመጠየቅ ልበ ሙሉነት እንዲቀዳጁና ራሳቸውን እንዲገልጹ ይረዳቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ጥናቱ አረጋግጧል። ወላጆች የአሁኑን ሁኔታ የቅድመ መደበኛ ት/ቤት መርሃ ግብር ተጠቃሚ ካልሆኑ፣ ደካማ የቋንቋ ክህሎት ከነበራቸውና ለ1ኛ ክፍል በአግባቡ ዝግጅት ካላደረጉ የቀድሞ ትላልቅ ልጆቻቸው ጋር አነጻጽረውታል (Tiumelissan and Berhanu forthcoming)።

ዜሮ ክፍሎች፣ በተለይ ለዚሁ ዓላማ ከሰለጠኑ መምህራን ጋር መገኘታቸው እንደ በጎ ለውጥ የተወሰደ ሲሆን በሌላ በኩል፤ ወላጆች፣ መሰረተ ልማቶቹንም ሆነ መምህራኑን በተመለከተ ስጋቶቻቸውን ገልጸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ወላጆች ት/ቤቶቹ፣ ለሕጻናቱ በጣም ሩቅ ናቸው ብለው ያምናሉ፤ በአማራ ክልል አንድ ት/ቤት መንገዱ አቀበታማና ቁልቁለታማ በመሆኑ ት/ቤት ለመሄድ አስቸጋሪ አድርጎታል፤ ሌላው ት/ቤት ደግሞ ሕጻናት አደገኛ መንገድ ማቋረጥ የሚጠበቅባቸው ሲሆን አራት ሕጻናትም በአደጋ መሞታቸው ተነግሯል። የዜሮ ክፍል መማሪያዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቱ ባልተለዩባቸው ት/ቤቶች ውስጥ የትናንሽ ህጻናትን ጥበቃና ደህንነት በተመለከተ ሥጋቶች ተፈጥረዋል። በኦሮሚያ አካባቢ እናቶች፣ የዜሮ ክፍል መማሪያዎች ከቀረው ት/ቤት ባለመታጠራቸውና ሕጻናቱን የሚጠብቅ ዘበኛ ባለመኖሩ ጭንቀት አድሮባቸው ነበር።

በዜሮ ክፍል መሰረተ ልማቶች ረገድ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከተማ አካባቢ በሚገኙ የግል መዋዕለ ሕጻናትና በአማራ ክልል በአንደኛው ት/ቤት ጥሩ መሰረተ ልማቶች መኖራቸው ተስተውሏል። ሆኖም ወላጆች በአጠቃላይ ስጋቶች እንዳሉባቸው ገልጸዋል። እነዚህም የመማሪያ ክፍሎች አነስተኛ መሆንና የህጻናት በአንድ ክፍል ውስጥ መጨናነቅን ያካትታሉ፤ ለምሳሌ፤ በኦሮሚያ አካባቢ፣ ከ20-25 ለሚደርሱ ሕጻናት በተዘጋጀው ክፍል ውስጥ ከ40-45 ሕጻናት እንደነበሩ፣ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ተናግሯል። በአንዳንድ ሁኔታዎች መስኮቶቹ አነስተኛ ወይም በቂ የአየር ማስገቢያና ማስወጪያ የሌላቸው መሆናቸው ተስተውሏል። በአንድ የትግራይ ት/ቤት፣ የመማሪያ ክፍሉ የተወሰነ ክፍል በመጋዘንነት ያገለግል ነበር። ዴስኮችና ወንበሮች ብዙ ጊዜ ዕድሜን ያላማከሉ ሲሆኑ፣ በትግራይ የጥናት አካባቢ ሕጻናት በሽፍት ነበር የሚማሩት፤ አንደኛው ቡድን በዛፎች ጥላ ስር በድንጋያማ መሬት ላይ ተቀምጦ ሲማር፤ ሌላኛው ቡድን ደግሞ ለትላልቅ ህፃናት የተዘጋጁ ዴስኮች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ይማራል፤ በዚህም ሳቢያ ሕጻናት ቆመው መጻፍ ነበረባቸው። የመጻሕፍትና የመምህራን መምሪያ እጥረትም ተስተውሏል። በአማራ ክልል በሚገኝ አንድ ት/ቤት ግድግዳዎች ላይ ፖስተሮች ተለጥፈው የተስተዋሉ ሲሆን እነዚያ ፖስተሮች ግን ከዜሮ ክፍል ይልቅ ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የበለጠ ተገቢነት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። የመኝታ አካባቢዎችና ፍራሾች ችግር እንዲሁም በቂ የመጫወቻ ቁሳቁሶች ያለመኖር በእጅጉ አሳሳቢ ነበሩ፡፡ ተገቢና ዕድሜን ያማከሉ አስተማማኝ መፀዳጃ ቤቶች አለመኖርና የቧንቧ ውሃ ችግር እንደ ዋነኛ እንቅፋቶች ታይተዋል፡፡ በትግራይ አካባቢ፣ ሕጻናት ከት/ቤት ውጭ ከሚገኝ የጋራ የውሃ ጣቢያ ውሃ ይቀዳሉ ወይም በኋላ ከወንዝ ቀድተው የሚሞሉት ውሃ ከቤታቸው በፕላስቲክ መያዣዎች ወደ ት/ቤት ያመጣሉ።

ምናልባት ከሁሉም አሳሳቢው ጉዳይ የት/ቤት ምገባ አለመኖር ሲሆን በዚህም ሳቢያ ሕጻናት ከጠዋቱ አጋማሽ ክፍለ ጊዜ በላይ መቆየት አይችሉም፡፡ በኦሮሚያ አካባቢ፣ በቀደመው ዓመት፣ የት/ቤት ምገባ ነበር፤ ግን ቆሟል፤ ይህም እያደገ የመጣ የህጻናት ትምህርት ማቋረጥን አስከትሏል፡፡ በትግራይ አካባቢ የት/ቤት ምገባ ለመጀመሪያ ደረጃ ክፍሎች የታለመ ሲሆን የዜሮ ክፍል ሕጻናትም የምገባው ተጠቃሚ ተደርገዋል፤ አንዳንዶቹ ግን የሚቀርብላቸውን ገንፎ አልወደዱትም።

አብዛኞቹ መምህራን ዜሮ ክፍልን ለማስተማር ብቁ የሚያደርጋቸው የተለየ መደበኛ ሥልጠና ያልወሰዱ ናቸው የሚሉ ስጋቶችም ተንጸባርቀዋል። ብዙዎቹ መምህራን በዋናነት በዝቅተኛ ደሞዝ ሳቢያ በሥራቸው ደስተኞች አልነበሩም። በጊዜያዊነት የተቀጠሩቱ በመደበኛ መንገድ ብቃታቸው የተረጋገጠ ባለመሆኑ በት/ቤቱ የደሞዝ መክፈያ መዝገብ ውስጥ ያልተካተቱ ሲሆን ደሞዛቸውም ብቃታቸው ከተረጋገጠ መምህራን ከግማሽ በታች ያነሰ ነበር። ይህም ከፍተኛ መጠን ያለው የሥራ መልቀቅን አስከትሏል። በመምህራን እጥረት ሳቢያም ከትግራይ በስተቀር በሁሉም አካባቢዎች፣ ዕድሜያቸው ከ4-6 የሆኑ ሕጻናት በአንድ ክፍል ውስጥ ይገኙ የነበረ ሲሆን አንድ ዜሮ ክፍል ደግሞ መምህሩ ከሥራ መልቀቁን ተከትሎ ለመዘጋት በቅቷል። በኦሮሚያ፣ በከተማ አቅራቢያ ከወላጆቿ ጋር የምትኖር አንዲት ሴት መምህርት፣ ያለ ወላጆቿ ድጋፍ ወጪዎችዋን መሸፈን እንዳልቻለች ገልጻለች። ሌላዋ በትግራይ የምትገኝ ደግሞ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ ባለመሆኗ፣ በክረምት የዕረፍት ወቅት ደሞዟን እንዳላገኘች በምሬት ገልፃለች። ከአጭር ጊዜ የኮንትራት ተቀጣሪዎች መካከል የተወሰኑት ሌሎች ሥራዎች ነበራቸው፤ በአማራ ክልል በሚገኝ አንድ ት/ቤት ውስጥ ከመመሪያው በተቃራኒ፣ አንዱ ወንድ መምህር፣ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራና በበዓላትና በቅዱሳን ቀናት ብቻ የሚያስተምር ነበር። እንዲያም ሆኖ አንዳንድ ጠቃሚ ሥልጠናዎች እንደሚሰጡ የሚጠቁሙ መረጃዎች ተገኝተዋል። በትግራይ አካባቢ፣ መምህራን፣ የክረምት ሥልጠና መከታተል የቻሉ ሲሆን በአማራ አንዲት መምህር፣

8 ይህ ጥናት አንድ የከተማ አካባቢ እና ሦስት የገጠር አካባቢዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ የጥናት አካባቢም ከአንድ እስከ ሦስት ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ጥናቱ በወረዳ ከሚገኙ ባለሙያዎች፣ ከቀበሌ ካቢኔዎች፣ ከአባቶችና ከእናቶች ጋር የቡድን ውይይት ያደረገ ሲሆን፤ በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ከሚገኙ ሴትና ወንድ ተማሪዎች ጋር፣ እነሱ የነበሩበትን የትምህርት ሁኔታ ከአሁኑ ጊዜ ጋር ለማነጻጸር እንዲመች የቡድን ውይይት አድርጓል። ከትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራን እንዲሁም ከዜሮ ክፍል መምህራን እና አስተባባሪዎችም ጋር ጥልቀት ያላቸው የተናጠል ቃለ መጠይቆች ተደርገዋል።

የማስተማሪያ ድጋፎችን ለማዘጋጀት የሚያስችላትን ሥልጠና ወስዳለች።

የዜሮ ክፍል ትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ያግዛሉ ተብለው ከተጠቆሙ ከት/ቤት ጋር የተያያዙ መሰረተ ልማቶች መካከል፡- የታጠሩ አካባቢዎች፣ በቂ ስፋት ያላቸው የመማሪያ ክፍሎች፣ የአየር ማስገቢያና ማስወጪያ፣ ዕድሜን ያማከሉ ዴስኮችና ወንበሮች፣ የውሃና አስተማማኝ መፀዳጃ ክፍሎች ተደራሽነት፣ የቤት ውስጥና ከቤት ውጭ ጨዋታዎች፣ አጋዥ የትምህርት መርጃዎች፣ ለመኝታና ለመመገቢያ የሚሆኑ ክፍሎችና ፍራሾች፣ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕጻናትን ታላሚ ያደረጉ አገልግሎቶችና የት/ቤት ምገባ ይገኙባቸዋል። ለመምህራን የክረምትና ክህሎት ማጎልበቻ ኮርሶችን ጨምሮ የተሻለ ሥልጠናና ክፍያ እንዲሁም ማህበረሰብን በዓይነት፣ በገንዘብና በጉልበት የሚያሳትፍ የተሻለ የአቅም ማሰባሰብ ንቅናቄ በጣም ወሳኝ መሆኑ ታምኖበታል።

በተለይ በዜሮ ክፍል መርሃ ግብር አማካኝነት የተከናወነው ፈጣን የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ማስፋፋት፣ በቅድመ መደበኛ ት/ቤት ተደራሽነት ረገድ ከፍተኛ ዕድገትን አምጥቷል፤ በገጠርና ራቅ ባሉ አካባቢዎች፣ በታዳጊ ክልሎችና በድሃ ቤተሰቦች ለሚኖሩ ሕጻናት የተለዩ ጠቀሜታዎችን በማቀዳጀት። የዜሮ ክፍል የት/ቤት ዝግጁነትን የማሻሻል ዓላማ መሳካቱንና የሚጠበቁት የእኩልነት ጥቅሞች እውን መሆናቸውን ለማረጋገጥ ግን የመምህራንና አሳላጮች ሥልጠናን ማሻሻልና የመማሪያ ከባቢውን ማሳደግን ጨምሮ የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል ላይ የበለጠ ማተኮርን ይጠይቃል። የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ት/ቤት መርሃ ግብር በቂ ነው አይደለም የሚለው ጉዳይና የተጨማሪ ዓመታት ወጪዎች ሊሸፈኑ ይችላሉ ወይ የሚለው ተጨማሪ ጥናትን የሚፈልግ ነው። የዚህ ይዘት-ተኮር ዓይነተኛ ጥናት ጥልቅ ዕይታዎች መገምገም ያለባቸው፣ በECD ላይ ተጨማሪ የትንተና ሥራና የጥቆማ ሃሳቦቹ የሚኖራቸው አንደምታ ተጨማሪ ውይይት ይፈልጋሉ በሚል አውድ ነው።

## References


Ministry of Education (MoE) (2018) 'Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016-17 G.C.)', Addis Ababa: EMIS and ICT Directorate, Ministry of Education, Federal Democratic Republic of Ethiopia.

Orkin, K., W. Yadete, and M. Woodhead (2012) *Delivering Quality Early Learning in Low-Resource Settings: Progress and Challenges in Ethiopia,* Working Papers in Early Childhood Development 59, The Hague: Bernard van Leer Foundation.

Rossiter, J. (2016) Scaling Up Access to Quality Early Education in Ethiopia: Guidance from International Experience, Young Lives Policy Paper 8, Oxford: Young Lives.

Tiumelissan, A., and K. Berhanu (forthcoming) *The Contribution of O-Class Within the Broader Context of Early Learning Resources and Opportunities in Selected Young Lives sites in Ethiopia,* Young Lives Working Paper, Oxford: Young Lives.

Woldehanna, T. (2016) 'Inequality, Pre-primary Education and Cognitive Development in Ethiopia: Implication for Public Investment in Preschool Education', International *Journal of Behavioral Development* 40.6: 509-516.

Woldehanna, T., and M. Araya (2017) *Early Investment in Preschool and Completion of Secondary Education in Ethiopia: Lessons from Young Lives,* Young Lives Working Paper 168, Oxford: Young Lives.

Woodhead, M., J. Rossiter, A. Dawes, and A. Pankhurst (2017) *Scaling-up Early Learning in Ethiopia: Exploring the Potential of O-Class,* Young Lives Working Paper 163, Oxford: Young Lives.


### ይሂ አጭር የጥናት መግለጫ


ከዩኒሴፍ ኢትዮጵያና ከህጻናት ኢንቨስትመንት ፋውንዴሽን ፈንድ (CIFF) ጋር በትብብር የተዘጋጀው ይህ አጭር የጽሑፍ መግለጫ 'Improving the evidence for early intervention: using cohort research to improve policy in Ethiopia and India' በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ በያንግ ላይቭስ የጥናት ውጤት ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ የገንዘብ ድጋር ከCIFF አግኝቷል።

ይህ አጭር ጽሑፍ በያንግ ላይቭስ እና በዩኒሴፍ ከተሰሩ አምስት ጽሑፎች ውስጥ አንዱ ነው። እነዚህ ጽሑፎች በያንግ ላይቭስ አለም አቀፍ ድረ ገጽ (www.younglives.org.uk)፤ በያንግ ላይቭስ ኢትዮጵያ ድረ ገጽ (www.younglives-ethiopia.org) እንዲሁም በዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ድረ ገጽ (https://www.unicef.org/ethiopia) ላይ ይገኛል።`

ያንግ ላይቭስ፤ በአራት አገራት (ኢትዮጵያ፣ ህንዴ፣ ቬትናምና ፔሩ) በሚገኙ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ መካከል የተፈጠረ የትብብር አጋርነት ነው፡፡ ያንግ ላይቭስ፤ በዋናነት በእንግሊዙ ዓለማቀፍ የልማት ተቋም (DFID) ሲደገፍ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ፣ ያንግ ላይቭስ ከቀድሞው የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ተቋም (EDRI) እና ፓንክረስት የልማት ጥናት አማካሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (PDRC) በትብብር ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህ አጭር የጥናት መግለጫ ውስጥ የተንጸባረቁት አመለ`ካከቶች፤ የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ፣ DFID፣ ዩኒሴፍ፣ CIFF ወይም የሌሎች ድጋፍ ሰጪዎችን አቋም አይወክሉም።